# ፓስተር ዳንኤልና መጥምቁ ዮሐንስ

*መክብብ ማሞ*

ከመጥምቁ ልጀምር - ዮሐንስ ይባላል። የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት አካባቢ የኖረ ነበር ፣ የጌታችን የቅርብ ዘመድም ነበር። ዮሐንስ በጣም ሃቀኛ ሰው ነበር - በወቅቱ ያውጅ የነበረውም መልዕክት ኃይለኛ። ሁሉንም «ንስሃ ግቡ» ይል ነበር። «ሁሉንም» ማለት ሁሉንም ወጣቶች ፣ አረጋውያንን ፣ የሮም ወታደሮችን ፣ ካህናትን ፣ ፈሪሳውያንን ፣ የሮም ባለሥልጣናት ፣ ገዢዎች . . . ኑሮው በረሃ ፣ ምግቡ አንበጣና የበረሃ ማር ፣ ልብሱም የግመል ጠጉር ነበር። በዚያን ዘመን የገሊላ ገዢ የነበረው ሄሮድስ አንቲጳስ የወንድሙን ሄሮድስ ፊሊጶስን ሚስት ሄሮዲያዳን አግብቷት ነበር። ይህንን ሕገወጥ ተግባር የተመለከተው መጥምቁ ሄሮድስን በቀጥታ እንዲህ ነበር ያለው «የወንድምህን ሚስት እንድታገባ ሕግ አይፈቅድልህም።» መጥምቁ እንዲህ ያለ ሰው ነበር - እቅጩን ፊትለፊት የሚናገር። «ገዢ ከሆንክ ፣ ሕገ እንዲከበር ከፈለግህ ፣ ተገዢዎችህም ይህንን ሕግ እንዲያከብሩ ከፈለግህ ፣ ምናልባት ዘንግተኸው ከሆነ ሕጉ የሚለውን እነግርሃለሁ። የወንድምህ ሚስት ሄሮዲያዳ ያንተ አይደለችም። እርሷን እንድታገባ ሕግ አይፈቅድልህም» ነበር ያለው።

ይህንን ቀጥተኛና አስደንጋጭ መልዕክት በተደጋጋሚ የሰማው ሄሮድስ የሚያደርገውን ቢያጣ መጥምቁን እስር ቤት ወረወረው። ሆኖም መንፈሱ እረፍት አላገኘም። ምክንያቱም መጥምቁን ሲያስር ራሱንም ጭምር ነበር እስር ቤት የከተተው። ዕረፍት የሚያስገኝለት ተግባር «ሕግ ይከበር» የሚለውን ማሰር ሳይሆን ሕጉን ማክበር እንደሆነ ሊቀበለው የማይችል ሃቅ ሆነበት። ቀጥሎም የልደት በዓሉን ያከብር በነበረበት ወቅት የሄሮዲዳ ልጅ በዳንስ ልቡን ስታማልል በገዢዎች ፊት የገባላትን ቃልኪዳን ለማክበር ሲል የመጥምቁን ራስ እንዲቆረጥ አስደረገ። ለእውነት ፣ ለሃቅ ፣ ለቃል የሚከፈል ፍጹም መስዋዕትነት ይሏል ይህ ነው።

ከሁለት ሺህ ዓመታት ወደዘመናችን ፣ ከገሊላም ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ መጥምቁን አናገኝም - ፓስተር ዳንኤል ገብረሥላሴን እንጂ። የቅንጅት አመራሮች ለእስር በተዳረጉበት ወቅት እነርሱን ለማስፈታት በተደረገው ፖለቲካዊ ሽምግልና ፓስተሩ በዋንኛነት ተሳትፏል። «ለዘመናት የቆየውን የኢትዮጵያን የሽምግልና ተቋም ያዋረደ» በተባለለት ድርድር ውስጥ የነበረው ፓስተር Justice for All - Prison Fellowship Ethiopia የተባለ ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ሲሆን ስለእስረኞቹ አፈታት ግልጽ የሆነ ማብራሪያ ሳይሰጥ ቆይቶ እንደ ሄሮድስ በቅዠት ሲባንን የነበረው ወዲዜናዊ የኢትዮጵያን ተስፋ መልሶ ወደ እስር ቤት በወረወረ ጊዜ «ድርጊቱ አግባብ አይደለም» ለማለት ሳይችል ይኸው ዓመት አልፎታል።

ይህም አልበቃ ብሎት ሰሞኑን ደግሞ በኢትዮጵያ ስለሚገኙ እስርቤቶችና ታሳሪዎች እንዲሁም ስለቃሊቲ እስርቤት «አጃኢብ!» የሚያሰኝ ቃለመጠይቅ ሲሰጥ ሰማነው። በተጭበረበረ የቪዲዮ ቀረጻ ለዓመታት «የዳበረ ልምድ» ያለው ወያኔ አሁንም ይህንን ልምዱን በእስረኞች ዙሪያ ተግባራዊ በማድረግ ሕዝብን ለማታል መሞከሩ ምናልባት «ሊያምኑኝ የሚችሉ ጥቂት የዋሆች ይኖራሉ» ብሎ ካላሰበ በስተቀር ሌሎቻችንንስ ምንም ቢሆን እንደማንታለልለት ሊገነዘብ ይገባዋል። ለዕርዳታ የተላከን ገንዘብ በጆንያ አሸዋ በመሙላት ሻጭና ገዥ ሆኖ በመቅረብ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ለጦር መሣሪያ መግዣ በማዋል የራሱን ሕዝብ እንዳስጨፈጨፈ በአለምዓቀፍ የመገናኛ ብዙሃን በማስረጃ የተዘገበና በቀድሞ አባሎቹ የተረጋገጠ ድርጊት ነው። ከዚህም ሌላ የሓውዜን ሕዝብ ለገበያ የሚወጣበትን ቀን ጠብቆ አስቀድሞ በየቦታው ተመቻችተውና ተረጋግተው በተቀመጡ የቪዲዮ ካሜራ ባለሙያዎች አሰቃቂውን እልቂት በመቅረጽ የፈጸመው ኢሰብዓዊ ድራማ የትግራይ ሕዝብ እንዲሁም መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘላለም የማይረሳው ነው።

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ታዲያ ይህንኑ ለዓመታት ሲከተል የቆየውንና ዘመን ያለፈበትን አሳፋሪ የቪዲዮ ቀረጻ ድራማ በእስርቤት መቀጠሉ «የተማረውን አለመርሳቱ» ይሆን ወይስ «ሁሉንም ሰው ሁልጊዜ እያታለልኩ» በማንአለብኝነት እገዛለሁ የሚል እብሪት ይሆን መልሱን ለራሱ እተወዋለሁ:: ወደ እስርቤቱ ተውኔት ስንመለስ ግን ልማታዊው ጋዜጠኛ ፓስተሩን እንዲህ በማለት ሲጠይቅ ይደመጣል «የኢትዮጵያ እስርቤቶች ሁኔታ እንዲሁም የታራሚዎች መብት ምን ይመስላል?» ፓስተሩም ይመልሳል «የእኛ አገር ስታንዳርዱ ከአፍሪካ ብቻ አይደለም ከሌሎች አገሮች ሲወዳደር በአንዳንድ ሁኔታ ከአቅም ማነስ ብቻ ካልሆነ በቀር የሰብዓዊ መብት አያያዛቸው የተሻለ ነው ብል ማጋነን አይሆንም:: . . . በየጊዜው ብቻ ሳይሆን በየቀኑ በእስርቤቶች ውስጥ ለውጥ አለ:: . . . እስረኞች በእኛ አገር በነጻ የመንቀሳቀስ መብት አላቸው:: . . . እኛም የእስረኞችን ጉዳይ በተመለከተ ከመንግሥት ጋር በመሥራት ሦስት ጊዜ ሽልማት አግኝተናል::. . . » እዚህ ላይ አንድ ሃሳብ መጣልኝ «ታዲያ ምነው ፓስተር ከመንግሥት ጋር በመሥራት እንደምንም ብላችሁ የኢትዮጵያን ተስፋ ከእስር አስፈትታችሁ ለ4ኛ ጊዜ ብትሸለሙ?!»

የሃይማኖት መሪዎች በመንፈሳዊው ብቻ ሳይሆን በዓለማዊው (መንግሥታዊ) ጉዳዮች ላይ ተሳትፎ በማድረግ ስለ ህግ መከበር ፣ ስለማኅበራዊ ፍትህ ፣ ስለሰው ልጆች እኩልነት ፣ ወዘተ ድምጻቸውን ሲያሰሙ ተጽዕኖ ከማድረግ አልፈው ሃሳባቸው ተቀባይነት እንዲኖረው የማድረግ ልዩ ተሰጥዖ አላቸው:: ለስጋቸው ያደሩ አይደሉም ተብሎ ስለሚታመን ንግግራቸው ተቀባይነት ያለውና ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ነው:: ቃላቸውን የሚሰማና ተግባራዊ የሚያደርግ ራሱን ነጻ ያወጣል ሕዝቡንም በሰላም ይመራል:: እንደ ሄሮድስ ሰላም የሚነሳው ደግሞ ራሳቸውን ይቆርጣል:: እዚህ ላይ ጀግናውን ሰማዕት አቡነ ጴጥሮስን ያስታውሷል::

መጥምቁና ፓስተሩ አንድ አምላክ አንድ ጌታ እናመልካለን ይላሉ:: መጥምቁ የሕግ የበላይነት ይከበር ሲል ፓስተሩ ግን ሕግ እንዳስፈላጊነቱ ሊከበር ወይም ሊሻር ይችላል ይላል:: መጥምቁ የመንግሥት ባለሥልጣንንም ሆነ ገዢን በግልጽ ፊትለፊት ያጠፋውን በመናገር «ተሳስተሃል» ሲለው ፓስተሩ ግን «ከመንግሥት ጋር በመሥራት» መሸለም የሃቀኝነት መለኪያ ነው ይለናል:: መጥምቁ በሃሰት ከምመሰክር ፣ እውነትን እያወቅሁ ዝም ከምል ህይወቴን እሰጣለሁ ሲል ፓስተሩ ግን እንዲህ ያለ ሞኝነት አያስፈልግም ተመሳስሎ መኖር ነው ተገቢው ነገር ይለናል:: መጥምቁ እውነት ነጻ ያወጣል እያለ ሲሰብክ ፓስተሩ ደግሞ «ለይቅርታ ቦርድ ጥፋተኛ ነኝ ብሎ መማጸን ነጻ ያስወጣል» ይላል::

ይህ የሰሞኑ የፓስተሩ ድርጊት ከመጽሃፍ ቅዱስ ላይ ሌላ ታሪክ አስታወሰኝ - በለዓም:: ከብዙ ሠራዊት ጋር እየገሰገሰ በመጣበት የእስራኤል ጦር የተደናገጠው የሞዓብ ንጉሥ «እስራኤልን እርገምልኝ» ብሎ ለበለዓም መልዕክት ከመማለጃ ብር (ጉቦ) ጋር አስይዞ ይልክበታል:: በለዓም ግን «እኔ የባረኩትን ሕዝብ ለመርገም እንዳትሄድ» ብሎ ያስጠነቀቀውን ያምላኩን ቃል ወደጎን በመተው ለገንዘብ ብሎ የራሱ ወገን ለመርግም ሄደ:: ይህ የበለዓም ታሪክ ለጊዜያዊ ጥቅም ተገዝተው በሃይማኖት ስም ነፍሰገዳይ አምባገነን መሪዎችን የሚደግፉ ፣ ምዕመኑም በሃይማኖት ሽፋን ፀጥለጥ ብሎና አፉ ዘግቶ በባርነት እንዲኖር የሚያደርጉ የሃይማኖት ብቻ ሳይሆን የሰብዓዊ ሞራላቸው ፈጽሞ የላሸቀ በኢትዮጵያ የሚገኙ የሃይማኖት መሪዎች ተምሳሌት ነው::

ፓስተሩ «አመልከዋለሁ ፣ አገለግለዋለሁ» የሚለው አምላኩ ምን ብሎ እንደተናገረው እርግጠኛ ባልሆንም «የኢትዮጵያ ተስፋ ወደእስር ቤት መግባቷ ተገቢ አይደለም ፣ መፈታት አለባት» የሚለው መልዕክት ትክክለኛ መሆኑን እንደሚያምን ጥርጥር የለኝም:: ቁምነገሩ ግን ፓስተሩ እንደ መጥምቁ «ሕግ ይከበር» በማለት ስለዕውነት ይቆማል ወይስ እንደ በለዓም ለመማለጃ ሲል እውነትን ረግጦና ሃቅን ንቆ «በልማታዊ ፓስተርነት» ይቀጥላል?

mekbma@yahoo.com

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com